በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ውስጥ ከውሃ ጋር የተዛመደ አደጋ ስጋት ቅነሳን የሚዳስሱ መርሆች

መሪዎች ፣ ውሳኔ ሰጭዎች እና ዜጎች በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ውስጥ ባሉ ሀገሮች እና ከተሞች ከውሃ ጋር የተዛመዱ[1] አደጋዎች መከሰታቸውን እንደሚቀጥሉ ማወቅ አለባቸው ። ለወቅታዊ ወረርሽኝ በልዩ ሁኔታ የተነደፉ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስትራቴጂዎች እና እርምጃዎች በአደጋው ለተጎዱ አካባቢዎች የበሽታው ወረርሽኝ ዋና ማዕከል ከመሆን ይከላከላሉ እንዲሁም ከአደጋዎች በፍጥነት እንዲያገግሙ ይረዳሉ ። የሚከተሉት መርሆዎች ለፖለቲካ አመራሮች ፣ ለአደጋ ስጋት ቅነሳ እና ለኮቪድ-19 ምላሽ ሥራ አስኪያጆች እንዲሁም ለሁሉም ባለድርሻ አካላት ስትራቴጂዎችን እና እርምጃዎችን ለመንደፍ ተግባራዊ ምክር ይሰጣሉ ። እነዚህ ውጥኖች ለወደፊቱ በማንኛውም ጊዜ ሊከሰቱ የሚችሉ የውሃ-ነክ አደጋዎችን በወረርሽኝ ስርም ቢሆን ለመፍታት ያስችላሉ ። መርሆዎቹ ከውኃ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አደጋዎች የሚዳስሱ ቢሆንም ለሌሎቹ የአደጋ ዓይነቶችም በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

አሁን ባለው የኮቪድ-19 ሁኔታ ውስጥ የኮቪድ-19 ኢንፌክሽኖችን ለማቃለል እና የታመሙትን ለማከም አፋጣኝ ትኩረት ተደርጓል ። ሆኖም የውሃ-ነክ አደጋዎች ስጋት ልክ እንደ ቅድመ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ እንደቀጠሉ ናቸው ። ለአደጋ ስጋት ቅነሳ ድንገተኛ ምላሾች እና በኮቪድ-19 የጤና እንክብካቤ ምላሾች መካከል መደራረብ እና መወሳሰብ በአንዳንድ ሀገሮች እና ከተሞች ላይ አሉታዊ ተፅእኖዎችን ሊያጎሉ ይችላሉ ።

በውኃ-ነክ አደጋዎች የተጎዱ አካባቢዎችን አዲስ የወረርሽኝ ማእከሎች ወይም መስፋፊያዎች እንዳይሆኑ ለመከላከል በአሁኑ ወረርሽኝ ውስጥ የሚከሰቱ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስትራቴጂዎችን መተግበር እና የቅድመ-ጥንቃቄ እርምጃዎችን መውሰድ ያስፈልጋል ። የሚከተሉት መርሆዎች ለፖለቲካ መሪዎች ፣ ለአደጋ ስጋት ቅነሳ እና ለኮቪድ-19 ሥራ አስኪያጆች እና ለሁሉም ባለድርሻ አካላት በጋራ ለሚከሰቱ አደጋዎች የተጎነኑ ተፅእኖዎችን በማስወገድ እንዴት መዘጋጀት እና ምላሽ መስጠት እንደሚችሉ ተግባራዊ ምክር ይሰጣሉ ። እነዚህ መርሆዎች ከውኃ ጋር ተያይዘው የሚመጡ አደጋዎችን ለመቅረፍ የተለዩ ቢሆኑም ለሌሎች የአደጋ ዓይነቶችም በተመሳሳይ ተፈፃሚ ይሆናሉ ።

መርህ 1- በወረርሽኝ ውስጥ የመሪዎችን የአደጋ ስጋት ቅነሳ ግንዛቤን ማሻሻል

መርህ 2- የአደጋዎችን እና የወረርሽኞችን ስጋት አመራር ማቀናጀት

መርህ 3- ንጹህ ውሃ ፣ ፍሳሽ እና የንፅህና አጠባበቅ እና አቅርቦትን ከአደጋ በፊት በአደጋ ጊዜና ከዚያ በኋላ በአሰተማማኝ ሁኔታ ማቅረብ

መርህ 4- የአደጋ ስጋት አስተዳደር ባለድርሻ አካላትን ከኮቪድ-19 ስጋት መከላከል

---

[1] *በዚህ ሰነድ ውስጥ ከውሃ ጋር የተዛመዱ አደጋዎች ማለት በውኃ የሚመጡ ሁሉም ዓይነት አደጋዎች ማለት ነው ። እነሱም ከባድ ዝናብ ፣ አውሎ ነፋሳት ፣ ጎርፍ ፣ ድርቅ ፣ የመሬት መንሸራተት ፣ የደለል ፍሰት ፣ ሱናሚ ፣ ከፍተኛ ማዕበል ፣ መጥለቅለቅ ፣ የበረዶ ግግር ጎርፍ እና የውሃ ብክለት አደጋዎች ናቸው ። ከተጎጂዎች ቁጥር አንፃር የውሃ ነክ አደጋዎች ከሁሉም አደጋዎች ከ 95% በላይ ይይዛሉ ። ካለፉት 1,000 ዋና ዋና አደጋዎች መካከል ከ 90% በላይ የሚሆኑት ከውሃ ጋር የተዛመዱ ናቸው ።*

መርህ 5- ውስን የሆኑ የህክምና ሀብቶችን ከአደጋ ተጽዕኖ መከላከል

መርህ 6- በአደጋ ምክንያት የተሰደዱትን ከኮቪድ-19 ስጋት መከላከል

መርህ 7- የኮቪድ-19 ታማሚዎችን ከአደጋ ስጋት መከላከል

መርህ 8- በኮቪድ-19 ምክንያት በእንቅስቃሴ ገደብ ስር ላሉ ከተሞች እና አካባቢዎች ልዩ የፍልሰት መመሪያን ማዘጋጀት

መርህ 9- በኮቪድ-19 ሁኔታ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ውድመትን ለማስወገድ ውጤታማ በሆነ መንገድ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተግባራትን ፋይናንስ ማድረግ

መርህ 10- ዓለም አቀፋዊ አብሮነትን እና ትብብርን በማጠናከር እነዚህን ተደራራቢ ተግዳሮቶች በመቋቋም ዓለማችንን በተሻለ ደረጃ መልሶ መገንባት

መረዳት የሚገባን የጎርፍ ወይም የድርቅ አደጋ ምላሽ እና ማቋቋም ስራዎች በኮቪድ-19 ምላሽ ይውሰሰባሉ በተመሳሳይ በኮቪድ-19 ውስጥ የአደጋ ምላሽ የተወሳሰበ ነው ፡፡

## መርህ 1- በወረርሽኝ ውስጥ የመሪዎችን የአደጋ ስጋት ቅነሳ ግንዛቤ ማሻሻል

- የውሃ-ነክ አደጋዎች በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስር ውስጥም በአገሮች እና በከተሞች ሊከሰቱ እንደሚችሉ ይወቁ ፡፡ ምንም እንኳን በአደጋ እና ወረርሽኝ በጋራ የተጎዱ አካባቢዎች ያሉ ሁኔታዎች ውስብስብ እና ግራ የሚያጋቡ ቢሆኑም ደረጃ በደረጃ ውሳኔ መስጠት እና እርምጃዎችን መውሰድ ጥቅም ይኖራቸዋል። ምንም እንኳን ተግባራት በጣም ግዙፍ እና የተወሳሰቡ ቢመስሉም ተስፋ አለመቁረጥ ነው ፡፡ የወረርሽኙን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ውሳኔዎችን መወሰን በተመሳሳይ የአደጋውን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የወረርሽኙን መከላከያ ውሳኔዎች መወሰን በኋላ ግራ መጋባትን ለማስወገድ ይረዳል፡፡
- የአደጋ እና የወረርሽኝ አስተዳደር ስትራቴጂዎችን እና ድርጊቶችን ቅንጅት ማረጋገጥ ፡፡ የአደጋ ስጋት ቅነሳ እና የኮቪድ-19 ባለሙያ ቡድኖችን አንድ ላይ በማሰባሰብ በተከታታይ ውይይታቸው እና በተቀናጀ ምክራቸው ላይ በመመርኮዝ ምክር መስጠት ፡፡ እነሱን በማማከር ወሳኝ ውሳኔዎችን ማድረግ ፡፡
- ከውኃ ጋር የተዛመደ አደጋ ሲከሰት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ሰራተኞችን መከላከልን ጨምሮ እንደ ሃይል ፣ ትራንስፖርት ፣ ውሃ እና ንፅህና ያሉ የበሽታዎችን መስፋፋት እና አብሮ የሚከሰቱ አደጋዎች ድምር ውጤቶችን ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑ የሕክምና መሰረታዊ አገልግሎቶችን በተቻለ ፍጥነት ይጠበቁ ወይም ይጠገኑ ፡፡ ለዚህም የአደጋ ስጋት ቅነሳ ሥራ አስኪያጆችን ለወሳኝ መሰረተ ልማት የአደጋ ጊዜ ዕቅድ ማዘጋጀት እና የማገገሚ ቁሳቁስ / መሳሪያዎች አቅርቦትን ማመቻቸት ያሉ ቅድመ እርምጃዎች እንዲወስዱ መጠየቅ ፡፡ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ሥራ አስኪያጆችን ሰራተኞች ሁልጊዜ በስራ ላይ ስለማይሆኑ እና የህዝብ ስራዎች በ ኮቪድ-19 ምክኒያት ሲታገዱ በአስቸኳይ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ሰራተኞች እና መሳሪያዎችን በፍጥነት ለማንቀሳቀስ የሚያስችል ስርዓት እንዲመሰረት መጠየቅ ፡፡
- የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስራ አስኪያጆችን ወረርሽኝ በተንሰራፋበት ሁኔታ የአደጋ ተጋላጭነት አያያዝ በተመለከተ ወዲያውኑ የሚተገበሩ ዕቅዶችን እንዲያዘጋጁ መጠየቅ ፡፡ ለሆስፒታሎች ፣ ለሕክምና ተቋማት እና

ለሠራተኞቻቸው መከላከል ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ። በኮቪድ-19 ስር ያለው የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዕቅድ የተወሰኑ የወንዶችን ፣ የሴቶች ፣ ወጣቶችን እና የህፃናትን ፣ አዛውንቶችን ፣ የአካል ጉዳተኞችን ፣ ስደተኞችን ፣ ተፈናቃዮችን እና እንደ ሀገር ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ፣ ሀገር-አልባ ሰዎች ፣ የቀን ሠራተኞች ፣ የመንደር ነዋሪዎች ፣ የጎዳና ተዳዳሪዎች እና ለኮቪድ-19 ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች እንደ ተጓዳኝ በሽታ ላሉባቸው ተደራሽ መኾን አለባቸው ። በኮቪድ-19 እና በአደጋዎች በተጎዱ ግለሰቦች ላይ የተደራጀ መረጃን ማለትም በጾታ ፣ በእድሜ ፣ በዘር ፣ ተጓዳኝ በሽታ ያለ / የሌለ እንዲሁም ከላይ በተጠቀሱት የተወሰኑ ቡድኖች መሰብሰብ የኮቪድ-19 እና አደጋዎችን ለመቋቋም ውጤታማና የተቀናጁ ዕቅዶችን ማውጣት ።

- የሲቪል መከላከል ባለሥልጣናት እና የድንገተኛ ጊዜ የሕክምና አገልግሎቶች ለኮቪድ-19 ምላሽ በሚሰጡበት ወቅት ተደራራቢ ሀላፊነቶቻቸውን በፍጥነት ለማመጣጠን አደጋን እና ኮቪድ-19ን በአንድ ጊዜ ለመፍታት የሚያስችል ድንገተኛ የአሠራር ዕቅድ እንዲኖራቸው ማድረግ ።
- በአደጋ ወቅት እና በኋላ ለዘላቂ የውሃ እና ንፅህና አቅርቦት የሰው ሃይል እና የፋይናንስ ሀብቶች ምደባን ከፍተኛ ትኩረት ይስጡ በተለይም የእጅ መታጠብ የኮቪድ-19 ስርጭትን ለመከላከል ወሳኝ አካል ነው ።
- በዚህ ሰነድ መርሆዎች ውስጥ የተካተቱትን ነጥቦች በብሔራዊ እና በማህበረሰብ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዕቅዶች ውስጥ ያካቱ ። የግል ዘርፎችን ጨምሮ ሁሉም የአደጋ ስጋት ቅነሳ ባለድርሻ አካላት በንግድ ሥራ ቀጣይነት እቅዶቻቸው (Business Continuity Plans) ውስጥ በዚህ መርህ ውስጥ ያሉትን ሀሳቦች እንዲያካቱ መጠየቅ ።

መረዳት የሚገባን በአደጋ ስጋት እና ኮቪድ-19 ቅነሳ ውስጥ ያሉ ተዋንያንን ማቀናጀት ውጤታማ እና ቀልጣፋ ምላሽ ለመስጠት ያስችላል ።

**መርህ 2- የአደጋዎችን እና የወረርሽኞችን ስጋት አመራር ማቀናጀት**

- የጤናውን ዘርፍ በተቀናጀ የአደጋ አያያዝ ስርዓት ውስጥ ሙሉ በሙሉ ማካተት ። የአደጋ ስጋት ቅነሳ አስተዳደርን በኮቪድ-19 መሠረት ለማጠናከር የሰንዳይ ማዕቀፍ እና ሌሎች የዓለም አቀፍ መመሪያዎች መሠረታዊ አቀራረቦችን ምሳሌ አደጋን ያማከሉ አቀራረቦችን፤ ሁሉን አቀፍ የድንገተኛ ጊዜ አያያዝ፤ ሁሉም-አደጋዎች ያቀናጀ አቀራረብ፤ አካታች ህዝብን እና ማህበረሰብን ማዕከል ያደረገ አቀራረብ፤ ዘርፈ ብዙና ሁለገብ ትብብር፤ በጠቅላላው የጤና ስርዓት ላይ የተመሠረተ አቀራረብና ሥነ ምግባራዊ ግምት ይጠቀሙ ። የባዮሎጂካል አደጋዎችን ጨምሮ ሁሉንም ዓይነት አደጋዎች የመቋቋም አቅምን ለማሻሻል የአደጋ ስጋት ቅነሳ ትብብር እና የድርጊት ፕሮቶኮሎች መገምገም እና መስተካከል አለባቸው ።
- በኮቪድ-19 ሁኔታዎች ውስጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በከባድ ዝናብ ፣ በጎርፍ ፣ በአውሎ ንፋስ እና በቶርኔዶ የተከሰቱ ጉዳዮችን በፍጥነት ያጋሩ እና ይማሩባቸው። ከእነኚህ ትምህርቶች ውስጥ አብዛኛዎቹ በዚህ መርሆዎች ውስጥ ተንፀባርቀዋል ።
- የማህበራዊ ፣ ባህላዊ ፣ ጂኦግራፊያዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የሚያንፀባርቁ በኮቪድ-19 ሁኔታዎች ውስጥ የአደጋ ስጋት ቅነሳ አቀራረቦች ላይ የሚያጠነጥኑ ሁኔታ-ተኮር መመሪያዎችን እና ዌቢናሮችን ይፍጠሩ ። በኮቪድ-19 ሁኔታ ስር ከውሃ ጋር የተዛመዱ የአደጋ መከላከል ልምምዶችን በአደጋ ስጋት ቅነሳ አስተዳዳሪዎች እና ባለድርሻ አካላት ለማካሄድ ያስቡ ።

- አደጋዎች ከመከሰታቸው በፊት ለሆስፒታሎች እና ለጤና ተቋማት የአደጋ ስጋት ካርታዎችን እና የአደጋ ስጋት ቅነሳ ምክሮችን መስጠት ። የተቀናጀ የአደጋ ካርታዎችን / በኮቪድ-19 የተጎዱ አካባቢዎችን እና ተቋማትን የሚያሳይ ማዘጋጀት ። ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች የሚጎበኙ ጉብኝቶችን በማስወገድ የኢንፌክሽንም ሆነ የአደጋ ስጋት ሊቀንስ ይችላል ። የአደጋው ካርታዎች እንዲሁ በአደጋ እና በወረርሽኝ ሁለት ተጽዕኖዎች ምክኒያት በቤተሰብ ደረጃ የውሃ አቅርቦት አለመረጋጋት የተከሰተባቸውን ማካተት አለባቸው ።
- ነባር የቅድመ-ማስጠንቀቂያ እና ከአደጋ ቦታ የማስወጣት ስርዓቶችን በኮቪድ-19 ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ የማስወጣት እና ኢንፌክሽኑን ለመከላከል የሚያስችላቸውን መስፈርት እንዲያሟሉ መከለስ እና ማሻሻል ። በእንቅስቃሴ ገደቦች እና መመሪያ ውስጥ ከተፈጥሮ አደጋው የማስወጣት እና ሌሎች የምላሽ አይነቶች ጋር የሚዛመዱ አጭር እና ግልጽ የ "ቅድመ ማስጠንቀቂያ" የግንኙነት መልዕክቶችን ማዘጋጀት ።
- የአደጋ ስጋት ቅነሳ እና ኮቪድ-19 የጋራ የስጋት ግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻዎችን ማካሄድ ። የመከላከል እርምጃዎችን በመተግበር እና ለአደጋዎች የመቋቋም አቅምን ለማሳደግ እውቀትን በማዳበር የጤና ወረርሽኝን ጨምሮ ለአደጋ ተጋላጭዎች ከአደጋ የመቋቋም እሴት ግንዛቤን ማሻሻል ። በከፍተኛ ተጋላጭ ዞኖች ውስጥ በጋራ የሚከሰቱ አደጋዎችን የአደጋ ግምገማ እና የግንኙነት ሥራ ማካሄድ ።
- የአደጋ አስተዳደር ቡድኖች የአደጋ ውጤት እና ምላሾች የኮቪድ-19 ጉዳዮችን ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶችን በግልፅነት መያዛቸውን ማረጋገጥ ። ህብረተሰቡ እና በአደጋው የተጎዱ ወገኖች ትክክለኛ እና የቅርብ ጊዜ መረጃ ማግኘት መቻል አለባቸው ። የአደጋዎች አስተዳደር ቡድን ፍላጎቶችን (በመረጃ ላይ የተመሠረተ) እና የእርዳታ አቅርቦትን ከሕዝብ ጋር በማዛመድ ማኅበራዊ ትብብርን ለማጎልበት አመቻች መሆን አለበት ። የእርዳታ አቅርቦት በፍጥነት ከፍላጎቶች ጋር እንዲዛመድ የሚያስችል የትብብር መድረክ መፍጠር ።
- የወጣቶች ባህሪ አደጋን ለመቆጣጠር ወሳኝ አካል በመሆኑ የኮቪድ-19 ስርጭትን ለማስቀረት የአብሮነትን እና የትብብር ጥሪ ለማድረግ ነባር የወጣት ቡድኖችን ለአደጋ ስጋት ቅነሳ ማሰማራት ። በኮቪድ-19 ወረርሽኝ የአደጋ አያያዝ ፣ እፎይታ እና የመልሶ ማቋቋም እንቅስቃሴዎች ውስጥ ከወጣት ቡድኖች ጋር በመተባበር ልዩ ችሎታዎቻቸውን ለምሳሌ በአይሲቲ (ICT) ፣ ፈጠራ እና የአካባቢያቸውን ነዋሪዎችና እኩዮቻቸውን ለማንቀሳቀስ መጠቀም ።

መረዳት የሚገባን የውሃ አቅርቦት፣ ፍሳሽ እና ንፅህና ኮቪድ-19ን ለመከላከል እና ከአደጋዎች በፍጥነት ለማገገም ወሳኝ አካል መሆናቸውን ነው ።

### መርህ 3- ንጹህ ውሃ ፣ ፍሳሽ እና የንፅህና አጠባበቅ እና አቅርቦትን ከአደጋ በፊት በአደጋ ጊዜና ከዚያ በኋላ በአሰተማማኝ ሁኔታ ማቅረብ

- የተፈጥሮ አደጋዎች ብዙ ጊዜ የውሃ አቅርቦቶች ላይ መስተጓጎል በማስከተል የኮቪድ-19 ቅነሳ ጥረቶች ላይ ተጽዕኖ ሊያሳርፉ ይችላሉ። ከፍተኛ የውሃ እጥረት ባለባቸው ክልሎች የተፈጥሮ አደጋዎች ከሰው ወደ ሰው የሚተላለፍውን የኮቪድ-19 ቫይረስን ለመከላከል የሚረዱ እንደ የእጅ መታጠቢያ አተገባበርን እና የቆሻሻ አያያዝ አሰራሮችን ሊነኩ ይችላሉ ። የውሃ እጥረት የንፅህና አጠባበቅ ቀውሶችን ለመቆጣጠር የሚደረገውን ጥረት ሊያደናቅፍ ስለሚችል በተለይ በድርቅ ለተከሰቱ አደጋዎች ልዩ ትኩረት መደረግ አለበት ።

- የውሃ መሠረተ ልማት በተለይም የውኃ ምንጮችን ከብክለት መጠበቅ ። የውሃ ማቆርን ጨምሮ ያልተበከሉ የውሃ ምንጭ አማራጮችን መጠቀም እና የአደጋ እና ወረርሽኝ አደጋዎችን ለመከላከል የቆሻሻ ውሃ እንደገና ጥቅም ላይ መዋልን ዋስትና ማጤን ።
- የውሃ አገልግሎት ሰጭዎች የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዕቅዶችን በተፈጥሮ አደጋዎች ብቻ ሳይሆን በወረርሽኝ ላይም የሚያስከትሉትን ውጤቶች ማካተት አለባቸው ። ወረርሽኞች በሠራተኞች ላይ እና የውሃ አገልግሎት አቅርቦት ጥራት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ። የንፅህና አጠባበቅ ማስተዋወቂያ በሁሉም የሂደቱ ደረጃዎች ማለትም በሕክምና ማዕከሎች ፣ የውሃ / የአካባቢ ጽዳትና የግል ንፅህና አጠባበቅ ተደራሽነት እና የድንገተኛ ሰራተኞች በመሳሰሉ ውስጥ መካተት አለባቸው ።
- በቫይረሱ በተያዙት ማህበረሰቦች የቆሻሻ ውሃ ፍሳሾች ውስጥ በተለይም የአደጋ ጊዜ ስጋቶችን ለመከላከል የኮቪድ-19ን ዱካ ለመለየት የምርምር እና የዳሰሳ ጥናቶችን መደገፍ ። እንደ የፍሳሽውሃ-ተኮር ኤፒዲሚዮሎጂ (wastewater-based epidemiology) ያሉ አዳዲስ የምርምር አቀራረቦች መመርመር አለባቸው ። ኮቪድ-19 በውሃ እና ፍሳሽ ማስወገጃ መስመሮች ሊሰራጭ እንደሚችል ለማወቅ ውጤታማ እና ፈጣን መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ ።
- የውሃ አገልግሎት ድርጅቶች በንግድ ቀጣይ እቅዳቸው (Business Continuity Plans) ውስጥ የዲጂታል መሳሪያዎች እና የሪሞት አሰራር / ቁጥጥር ስርዓቶች ሚናን እንዲያሳድጉ መጠየቅ ። ሁሉም በተለይ የውሃ እና ፍሳሽ ማስኬጃ ቡድኖች ፣ የመቆጣጠሪያ ማዕከላት እና የላቦራቶሪ ሰራተኞች በኮቪድ-19 ስር የሚቻል ከሆነ በርቀት መሥራት አለባቸው ። በመስኩ ውስጥ ላሉት ሠራተኞች የኳራንቲን ዑደቶችን ከግምት ውስጥ የሚያስገቡ ልዩ ልዩ የሥራ ፈረቃዎችን መመደብ አለባቸው እና የኮቪድ-19 የግል መከላከያ መሣሪያዎች (Personal Protection Equipment (PPE)) ማግኘት አለባቸው ።

መረዳት የሚገባን በወረርሽኝ ወቅት ወሳኝ መሠረተ ልማት እና የሰው ሀብቶች ለጎርፍ እና ድርቅ ምላሽ እና መልሶ ማቋቋም አስፈላጊ መሆናቸውን ነው ።

### መርህ 4- የአደጋ ስጋት አስተዳደር ባለድርሻ አካላትን ከኮቪድ-19 ስጋት መከላከል

- ለአደጋ ስጋት ቅነሳ ባለድርሻ አካላት ስለ ኮቪድ-19 ማስተማር እና አቅማቸውን በስልት መገንባት ። ለአደጋ አስተዳደር ባለሥልጣናት እና በጎ ፈቃደኞች ከበሽታ መከላከልን በተመለከተ ተደራሽ ፣ አጭር እና ግልጽ መመሪያን ማቅረብ ። ለምሳሌ የምክር በራሪ ወረቀቶችን ፣ የዌብናር አቅርቦትን እና ሌሎችንም ይጠቀሙ ። በአደጋ ስጋት ቅነሳ መመሪያዎች እና በየቀኑ የስራ ዝርዝር ተግባራት ውስጥ የማህበራዊ ርቀት መመሪያዎችን ማካተት ።
- በጎ ፈቃደኞችን ጨምሮ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ባለድርሻ አካላት በአደጋ ዝግጅት / በመከላከል / በማገገም ሥራዎች ላይ ሲሰማሩ እንደ ጭምብል ያሉ መደበኛ የኮቪድ-19 መከላከያዎች መያዛቸውን ያረጋግጡ ። ከተቻለ በጣም ተላላፊ በሆኑ ሁኔታዎች ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ የኮቪድ-19 የግል መከላከያ መሣሪያዎችን (Personal Protection Equipment (PPE)) ያከማቹ ። በወረርሽኝ ሞገዶች መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ለሕክምና ላልሆኑ ፍላጎቶች የተትረፈረፈ የግል መከላከያ መሣሪያዎች (PPE) አቅርቦት በሚኖርበት ጊዜ ለአደጋ ስጋት ቅነሳ ሠራተኞች ማከማቸት ውጤታማ ይሆናል ።

- የአደጋ አስተዳደር ሠራተኞች ከሥራ ባልደረቦቻቸው እና ከተፈናቃዮች ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ሊመጣ የሚችል በሽታን ለመከላከል በየቀኑ የግል-ሕክምና ምርመራዎች እንዲደረጉ መጠየቅ ፡፡
- በጎ ፈቃደኞችን ጨምሮ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ባለድርሻ አካላት ሲጓጓዙ ፈጣን የአደጋ መከላከል / ማገገም አስፈላጊነት እና በኮቪድ-19 በተጎዱ አካባቢዎች እና በበሽታው ባልተጎዱ ሰዎች መካከል የበሽታ ስርጭትን የማስቀረት አስፈላጊነት ሚዛናዊ መሆን አለበት ፡፡
- የሚመለከታቸው ባለሥልጣናት ውሸባ (Quarantine) ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ የአደጋዎች ክትትልና የማስጠንቀቂያ ጥራት ተጽዕኖ ሊያድርበት ስለሚችል ጥራቱ መጠበቁን ማረጋገጥ ፡፡

**መርህ 5- ውስን የሆኑ የህክምና ሀብቶችን ከአደጋ ተጽዕኖ መከላከል**

- ሆስፒታሎችን እና የህክምና ተቋማትን ለመጠለያ በታ ከመጠቀም መቆጠብ ፡፡ እነዚህን ሕንፃዎች እና ተቋማት በአደጋ ጊዜ ካርታዎች እና በአደጋ ስጋት ቅነሳ እቅዶች ውስጥ ለመጠለያ በታዎች ከተሰየሙ ማስወገድ ፡፡
- የሕክምና ባልደረቦችን ፣ ተቋማትን እና መሣሪያዎችን ከአደጋ ተጽዕኖ ለመከላከል በሚከተሉት ሁኔታዎች ቅድሚያ መስጠት፡
    - አስፈላጊ የኃይል ማመንጫ መሣሪያዎችን ከውኃ ጋር ተያይዘው ከሚከሰቱ አደጋዎች (ጎርፍ ወዘተ) ለመጠበቅ ወደ ደህና አካባቢዎች ማሸጋገር እንዲሁም ረዳት የኃይል አቅርቦት መሣሪያዎችን ለሆስፒታሎች ፣ ለጤና ኬላዎችና ለሕክምና ተቋማት መስጠት ፡፡
    - የአደጋ ስጋት ቅነሳ ምክር ግንኙነትን ለማስኬድ ተገቢውን የአደጋ ምላሽ ሰራተኞች ወደ ሆስፒታሎች ፣ ጤና ኬላዎች እና ህክምና ተቋማት በፍጥነት መላክ ፡፡
    - በመጀመርያ ደረጃ አስፈላጊ የሕክምና መሣሪያዎችን እና ቁሳቁሶችን ወደ ላይኛው ፎቅ ማዘዋወር ፡፡
    - ለታካሚዎች እና ለህክምና ሰራተኞች የተላላፊ በሽታዎች ዞኖችን ከግምት ውስጥ በማስገባት የማስወጫ ዕቅዶችን መፍጠር ፡፡
    - በአደጋዎች ምክንያት የውሃ አቅርቦት እና የንፅህና አጠባበቅ አገልግሎቶች ሲስተጓጎሉ ለሆስፒታሎች ፣ ለጤና ኬላዎች እና ለህክምና ተቋማት የውሃ ፣ የፍሳሽ እና የንፅህና አቅርቦት በቅድሚያ መስጠት ፡፡
    - ለወረርሽኙ ምላሽ የሚያስፈልጉ በጤና ተቋማት የተትረፈረፈ ጤናማ በታዎችን ለይቶ በማወቅ እንዲሁም እንደ ጎርፍ ጠቅ ባሉ ለአደጋ ተጋላጭ በሆኑ አካባቢዎች ተጨማሪ የአጭር ጊዜ ኮቪድ-19 ሆስፒታሎች እንዳይገነቡ መከላከል ያስፈልጋል፡፡
    - የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ኃላፊነት ያላቸውን የሕክምና ባልደረቦች አደጋ ከመከሰቱ በፊት መሠረታዊ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ዕውቀት እንዲኖራቸው ማስተማር ፡፡

መረዳት የሚገባን የተፈጥሮ አደጋዎች እና የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ጥምረት ወደ ከፍተኛ የሰው ሕይወት መጥፋት ሊያመሩን ይችላሉ ።

**መርህ 6- በአደጋ ምክንያት የተሰደዱትን ከኮቪድ-19 ስጋት መከላከል**

- መጠለያዎች ማህበራዊ ርቀትን እንዲያካትቱ ንፅህናን ማመቻቸት እና ጥሩ የመጠለያ አሠራሮችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የአደጋ ማቆያ ዕቅዶችን ወዲያውኑ መፍጠር ወይም መከለስ ። የጅምላ ኢንፌክሽንን ለመከላከል የማቆያ ህንፃዎች / ተቋማት በትክክል መናፈሳቸውን ማረጋገጥ ። ተፈናቃዮችን ከኮቪድ-19 ለመከላከል የተወሰኑ ፍላጎቶችን ማሟላት የሚያስችሉ ተጨማሪ ሕንፃዎችን እና ቦታዎችን ለምሳሌ ማህበራዊ ርቀትን እና ህመምተኞችን ራስን ለብቻ የሚለዩ ቦታዎች ለይቶ ማወቅ ። በተቻለ መጠን የኮቪድ-19 ህመምተኞች ማቆያ ስፍራዎች ከህክምና አገልግሎት ጋር እንዲሁም እራሳቸውን ችለው ላሉ ህመምተኞች በተለያዩ ሕንፃዎች / ተቋማት / መጠለያዎች ሊቆዩ ይገባል ።
- በተቻለ መጠን በማንኛውም ጊዜ እና ቦታ የመልቀቂያ ዘዴዎች ከታች ወደላይ እንዲሆኑ ማስተዋወቅ ። ይህ ማለት ደህንነቱ የተጠበቀ ከሆነ ወደ ማቆያዎቹ ወይም ወደ አካባቢው ህንፃ ሁለተኛ ወይም የላይኛው ፎቅ መውጣት ማለት ነው ። ይህም አደጋዎችን ለማስቀረት በሚለቁበት ጊዜ የሚያጋጥሙ ጉዳዮችን ለመቆጣጠር እና የማቆያ መጠለያዎች ውስጥ በቫይረሱ የመያዝ አደጋን ለመቀነስ በሰዎች ብዙም ጥቅጥቅ ያሉ እንዳይሆኑ ማድረግን ይጨምራል ። እንደ ሜዳማና ቆላማ አካባቢዎች ያሉ ከታች ወደላይ መውጣት በማይቻልባቸው አካባቢዎች ከአከባቢው ማህበረሰብ ጋር የማቆያ ህንፃዎችን ለመጨመር ፣ መጠለያዎች እና የማቆያ ስፍራዎች መጨናነቅን ለማስቀረት በቅድሚያ መወያየት ።
- በማኅበራዊ አካታች አካሄድ አስቀድሞ ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑት ለምሳሌ አዛውንቶች ፣ የአካል ጉዳተኞች ፣ እርጉዝ ሴቶች እና ሥር የሰደደ በሽታዎች ያለባቸውን ህመምተኞች ከማህበረሰቡ ለይቶ ማወቅ እና ቅድሚያ እንዲወጡ ማቀድ ።
- ለተፈናቃዮች በቂ ንፁህ ውሃ ፣ ሳሙና ፣ የንፅህና መጠበቂያ አገልግሎት እና የንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁስ ማቅረብ ።
- የሙቀት መጠን መመርመርን የመሳሰሉ መሠረታዊ የሕክምና ምርመራዎችን ማካሄድ ።
- ከአደጋ ተፈናቃዮች መካከል ማንኛውንም ከኮቪድ-19 ጋር ተዛማጅ የሆነ አድልዎና ማግለል ይከላከሉ ። የተሳሳተ መረጃ እና የሐሰት ዜና በአስፈሪ ሁኔታ በፍጥነት እና በስፋት እየተስፋፋ ስለመጣ በአደጋዎች እና በኮቪድ-19 ሁኔታ እና ተጽዕኖዎች ላይ ትክክለኛውን መረጃ ማሳወቅ እና ማሰራጨትን መቀጠል ።
- ዜጎች አደጋዎች ከመከሰታቸው በፊት የአደጋ ጊዜ ሳጥኖች ውስጥ ጭምብሎችን ፣ መጥረጊያዎችን ፣ ሳሙናዎችን ፣ ፎጣዎችን እና ቴርሞሜትሮችን እንዲያካትቱ ይምከሩ ።
- በወረርሽኙ ምክኒያት በቀላሉ ሊበከሉ ከሚችሉ ቁሳቁሶች ይልቅ ለገንዘብ ልገሳ ጥሪ ያቅርቡ ። በጥሬ ገንዘብ ምክኒያት በኮቪድ-19 የመያዝ አደጋን ለመቀነስ በሁሉም የአደጋ ስጋት ቅነሳ ክፍያ ልውውጥ የኤሌክትሮኒክ ገንዘብ ማስተላለፍን ማስተዋወቅ ።

## **መርህ 7- የኮቪድ-19 ታማሚዎችን ከአደጋ ተጋላጭነት መከላከል**

- የአደጋ ስጋት ቅነሳ እና ኮቪድ-19 የተቀናጀ ከፍተኛ ትኩረት መሰጠቱን ማረጋገጥ እና የሰውን ሕይወት በቀጥታ አደጋ ላይ ከሚጥሉ አደጋዎች መከላከል ፡፡
- በተላላፊ በሽታዎች የሕክምና ቁጥጥር መርሆዎች ላይ በመመርኮዝ ለኮቪድ-19 ቅነሳ የተቀናጁ እርምጃዎችን መረዳትና መውሰድ ፡፡ እነዚህ የሕክምና መርሆዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ -1) የኢንፌክሽን ምንጭን ማስወገድ፤ 2) የማሰራጫውን መንገድ መቁረጥ፤ 3) ተጋላጭ ቡድኖችን መከላከል ናቸው ፡፡
- ለኮቪድ-19 ህመምተኞች በግል ውሸባ (Quarantine) ወይም በተሰየሙ ተቋማት ውስጥ ራሳቸውን የመከላከያ ዕቅዶችን መፍጠር ማለትም የመገናኛ እና የመልእክት መንገዶች ፤ በአደጋ ጊዜ ደህንነታቸው ወደ ተጠበቁ የውሸባ (Quarantine) ተቋማት የመልቀቂያ ዕቅዶች እና ከተለቀቁ በኋላ የሕክምና ድጋፍ መስጠት ናቸው ፡፡

## **መርህ 8- በኮቪድ-19 ምክንያት በእንቅስቃሴ ገደብ ስር ላሉ ከተሞች እና አካባቢዎች ልዩ የፍልሰት መመሪያን ማዘጋጀት**

- በአደጋዎች ጊዜ ውጤታማ የማስፈር እና የደህንነት ዋስትና እንዲሁም የፍርሃት ድርጊቶችን ለመከላከል ለእንቅስቃሴ ዝግ በሆኑ አካባቢዎች ልዩ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መስጠት ፡፡
- ፍርሃትን እና የተጠናከረ የኢንፌክሽን ስርጭትን ለመከላከል በእንቅስቃሴ ገደብ ሁኔታ ውስጥ አካታች የአስቸኳይ ጊዜ ማጓጓዣ ዕቅዶችን ይፍጠሩ ፡፡ የአደጋ ምላሽ ዕቅዶች በጊዜ የተቃኘ አሰራር ላይ የተመሠረተ እና በተወሰኑ አካባቢዎች ውስጥ የተወሰኑ ገደቦችን ማንሳትን ማካተትን ከግምት ውስጥ ማስገባት አለባቸው ፡፡
- በእንቅስቃሴ ገደብ ጊዜ አደጋዎች ቢከሰቱ ደህንነታቸው የተጠበቁ አካባቢዎች እና የማስለቀቂያ መንገዶችን ለመለየት ከአከባቢው ባለሥልጣናት ጋር ቅንጅትን መፍጠር ፡፡

መረዳት የሚገባን በኮቪድ-19 ስር አደጋዎችን በአግባቡ መያዙ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትሪሊዮን ዶላሮችን ያድናል ፡፡

## **መርህ 9- በኮቪድ-19 ሁኔታ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ ውድመትን ለማስወገድ ውጤታማ በሆነ መንገድ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተግባራትን ፋይናነስ ማድረግ**

- ከአደጋ እና ከአየር ንብረት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን አደጋዎች ለመቋቋም የሚያስችል ድንገተኛ በጀት እና ገንዘብ ይኑር በተመሳሳይ በወረርሽኙ የፋይናንስ አቤቱታዎች ሙሉ በሙሉ በገንዘብ ይደገፉ ፣ ተደራራቢ አደጋዎች የማይቀለበስ የኢኮኖሚ ውድመት ሊያስከትሉ እንደሚችሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ፡፡ በአደጋዎች የምላሽ አሰጣጥ ላይ በፍጥነት ገንዘብ እንዲያገኙ ከባንኮች እና / ወይም ከኢንሹራንስ ኩባንያዎች ጋር የድንገተኛ ጊዜ ፋይናንስ ስምምነቶችን ማዘጋጀት ፡፡

- በኮቪድ-19 ሁኔታ ውስጥ በፍጥነት ለሚከሰቱ እና በርከት ያሉ ተለዋዋጭ አደጋዎችን ለማስቀረት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተዋንያኖች ማቀድ እና ምላሽ መስጠት የሚያስችላቸውን ተንቀሳቃሽ የገንዘብ ድጋፍ እና የገንዘብ አቅርቦት እንዲያገኙ ማድረግ ።
- በአደጋዎች እና በተዛማች ወረርሽኞች ላይ ለሚያስፈልጉ የሸቀጦች እና አገልግሎቶች ግዥን በተመለከተ በዋጋዎች ፣ በአቅራቢዎች ፣ በወቅቶች እና በግዢ ዝርዝር መረጃን በመያዝ በአለም አቀፍ ፣ በዲጂታል እና በመረጃ ላይ በተመሠረተ እቅድ የአደጋ ስጋት አያያዝ አቅሞችን ማዘመን ። እንደ የማምረት አቅም ማነስ ፣ ረዥም እና የተጨናነቁ የአቅርቦት ሰንሰለቶች እና የአቅርቦት እጥረት ተግዳሮቶችን ለመጋፈጥ እቅድ ማዘጋጀት ።
- የኮቪድ-19 ኢንፌክሽን በንክኪ ምክኒያት እንዳይስፋፋ በስልክ ላይ በተመሰረተ ዲጂታል ግብይት ፣ ምንዛሬ እና ዲጂታል የክፍያ ዘዴን ማበረታታት ለምሳሌ በምስራቅ አፍሪካ ለሚገኙ አደጋ ተጠቂዎች በቀይ መስቀል እንደተሰራጨው ።

መረዳት የሚገባን በጋራ የሚከሰቱ የኮቪድ–19 እና አደጋዎች ጋር የሚደረገውን ውጊያ ለማሸነፍ ከተናጠል ይልቅ ዓለም አቀፋዊ አብሮነት አስፈላጊ ነው ።

**መርህ 10- ዓለም አቀፋዊ አብሮነትን እና ትብብርን በማጠናከር እነዚህን ተደራራቢ ተግዳሮቶች በመቋቋም ዓለማችንን በተሻለ ደረጃ መልሶ መገንባት**

- ሜጋ-አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ በአደጋው እና በተጎዳው ሀገር ኢኮኖሚ ላይ ዓለም አቀፍ አመኔታን ላለማጣት ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን በተላበሰ ስነ ምግባር ስለ አደጋው እና ተፅእኖው ትክክለኛ እና ወቅታዊ መረጃን ለዓለም ማህበረሰብ በመደበኛነት ማጋራት ።
- በተወሰኑ አካባቢዎች ውስጥ የውሃ-ነክ አደጋዎች በቅድሚያ ለማስጠንቀቅ በዓለም ሚቲዎሮሎጂ ድርጅት እና በተባበሩት መንግስታት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ድርጅት (UNDRR) አማካኝነት በአየር ንብረት ሁኔታ / የአየር ንብረት ኤጀንሲዎችን በመጠየቅ በዓለም ዙሪያ ከኮቪድ-19 ግብረ-ኃይሎች ጋር በንቃት እንዲተባበሩ እና ሊታወቁ ከሚችሉ የአየር ሁኔታ እና ከአየር ሁኔታ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አደጋዎች ትንበያ እንዲደርግላቸው መጠየቅ ።
- አስፈላጊ ከሆነ ዓለም አቀፍ የአደጋ ስጋት ቅነሳ እና የሰብአዊ ድጋፍ ሠራተኞችን እና መሣሪያዎችን ለማመቻቸት መዘጋጀት ። ዓለም አቀፍ የአደጋ ስጋት ቅነሳ እና የሰብአዊ እርዳታ ሰራተኞች እና መሳሪያዎች በተጠቁ አገሮች እና አካባቢዎችን በእንቅስቃሴ ገደቦች ወቅት ለመግባት የተቋቋሙ ልዩ ፕሮቶኮሎች ያስፈልጉ ይሆናል ። አገሮች በወረርሽኙ ወቅት ደህንነቱ የተጠበቀ ድጋፍ ለማግኘት እንደ ቪዛ አሰጣጥ ፣ የውሸባ (Quarantine) መውጫ እና የጉምሩክ ማጣሪያ እና ፕሮቶኮሎች ያሉ የማመቻቸት ዝግጅቶችን አስቀድሞ ማጤን እና ማቀድ አለባቸው ። የተላኩ ቡድኖች የመከላከያ ኪቶች ማዘጋጀት አለባቸው ። ወደ ኮቪድ-19 የተጎዱ አካባቢዎች ከመግባታቸው በፊት ለእነዚህ ዓለም አቀፍ ድጋፍ ቡድኖች የሕክምና መግለጫዎች መሰጠት አለባቸው ። በአለም አቀፍ የቀይ መስቀል እና የቀይ ጨረቃ ማኅበራት (IFRC) "ለአገር ውስጥ የአቅርቦት ማመቻቸት መመሪያዎች እና የአለም አቀፍ አደጋ እፎይታ እና የመነሻ መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ ደንብ (IDRL መመሪያዎች)" አጠቃቀም መሻሻል አለበት ።

- የአደጋ ስጋት ቅነሳን ምሳሌዎች በመከተል በወረርሽኝ ፖሊሲዎችና መመሪያዎች ላይ የተወሰኑ ክልላዊ ተቋማትን ስለማቋቋም መወያየት ። የእስያ ሀገሮች ለምሳሌ ይህንን የድንበር ተሻጋሪ ጉዳይ እና የክልል / ዓለም አቀፍ ትብብርን ቀጠናዊ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ማዕከልን በማቋቋም መፍትሔ አግኝተዋል ። ድንበሮችን እና ንግድን እንደገና ስለመክፈት በሚወያዩበት ጊዜ እና በፍጥነት በሚለዋወጡ ሁኔታዎች ውስጥ በጠንካራ አግባብ ውስጥ ያሉ አስፈላጊ ዕቃዎች እና ሰዎች አስፈላጊ ናቸው ።
- በአደጋዎች እና በሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ምክንያት ለሚፈልሱ ሰዎች እና ስደተኞች በኮቪድ-19 ምክኒያት መግቢያ ከመከልከል ይልቅ በልዩ ፕሮቶኮል እና እንክብካቤ የሚስተናገዱበት አግባብ ሊታሰብበት ይገባል ።
- አደጋዎች ከድንበር ወይም ከፖለቲካ ክልል አልፈው የሚከሰቱ በመሆኑ የአደጋዎችን ካርታ ከብዙ አመለካከቶች እና ትብብር ድንበር ተሻጋሪ በሆነ መንገድ ማዘጋጀት ። እንደ ውሃ ፣ ፍሳሽና የግል ንፅህና አጠባበቅ፤ ኃይል፤ ትምህርት፤ ጤና እና አመጋገብ፤ የመተዳደሪያ አቅረቦቶች፤ የልጆች እና ማህበራዊ ጥበቃ፤ መጠለያ እና መኖሪያ ቤት፤ እና የህዝብ ክፍት ቦታዎች ያሉ ዘርፎች ውስጥ መፍትሔዎችን መፈለግ ።
- በአጠቃላይ ሁሉም ከሁሉም በፊት እና ከሁሉም በላይ ለሀገራቸው ዜጎች ደህንነት እና መረጋጋት ቅድሚያ እንደሚሰጥ በመገንዘብ ወረርሽኙን ለመቋቋም ለሚታገሉ ዝቅተኛና መካከለኛ ገቢ ላላቸው ሀገሮች ዓለም አቀፍ ድጋፎችን ማቅረብ ። የአንዳችን ስጋት የሁላችንም ስጋት ነው ። ኮቪድ-19ን እና አደጋዎችን የመቋቋም ጥንካሬያችን በጣም ደካማ ከሆኑት እኩል ብቻ መሆኑን መገንዘብ።
- በድንበሮች እና በመንግስታት መካከል ስጋትን ለመረዳት እና ለመቀነስ የተቀናጀ እርምጃ መውሰድ ። ኮቪድ-19 የብሔራዊ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኤጄንሲዎችን ጨምሮ ሁሉንም የሚመለከታቸው የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን አቅም የሚያሟጥጥ የመንግሥታዊ አሠራር እንደሚያስፈልግ አሳይቷል ።
- ዓለማችንን በተሻለ መልሶ ለመገንባት የመልሶ ማቋቋሚ እቅድ አሁን ማውጣት መጀመር ። ብሄራዊ እና ክልላዊ መንግስታት በሀገራዊ እና አካባቢያዊ የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስትራቴጂዎች ውስጥ ባዮሎጂያዊ አደጋዎች እና ስጋቶች ላይ መስራት አለባቸው (የሴንዳይ ማዕቀፍ ዒላማ (e)) ። ለወደፊቱ አደጋዎች ሲያጋጥሙ የመንግሥት እና የግል ሥርዓቶች ጠንካራ እንዲሆኑ ለማድረግ በዚህ አደጋ የሚታዩት ተግዳሮቶች ለአዳዲስ ዕቅዶች እና ዲዛይኖች መሠረት ይሆናሉ ።